# አፍ -ሥግር ልብወለድ

በAsrat Yeshi T

## እንደመስፈንሪያ

ደራሲ አዳም ረታ ከ1977 ዓ.ም [ ከተደራሲው ጋር የተዋወቀበት እና በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ተከታታዮችና አንባቢዎች ልብ ውስጥ የመሠረት ድንጋይ ያስቀመጠበት "አባ ደፋር እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች" በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት የታተመው በ1977 ዓ.ም ነው ] ጀምሮ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ዉስጥ የራሱን ጡብ ለማስቀመጥ የቻለ ከያኒ ነዉ።በ1981 ዓ.ም ከታተመዉ "ማህሌት" ጀምሮ እስከ መጨረሻው ስራ" አፍ" ድረስ አዳም የራሱን ቀለም ሳይለቅ ነገር ግን አከያየኑ በይበልጥም አከያየኑ ዉስጥ ያለዉ ይዘት(content)፣ ቅርፅ( form)፣ አወቃቀር (structural) እና የአፃፃፍ ስልቱ እንዲሁም የስነፅሁፍ ፍልስፍናዉን በተለያየ ቴክኒኮች በመሞከር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየላቀ መምጣቱ ስራዎቹ ምስክር ናቸዉ። ለምሳሌ ከአጫጭር ልብወለድ ስራዎች "ማህሌት፣ከሰማይ የወረደ ፍርፍር" ስራዎች ላይ ቀጥተኛ አተራረክ(Linear Narrate) መንገድ ሲጠቀም የታሪክ ፍሰቱ መስመራዊ እንድርድሪት(Linear Momentum)፣ ከጭብጡ ረገድም ልል፣ ቃላት አጠቃቀሙም ጠና ያለ አለመሆኑን ከሌሎች ስራዎች አንፃር ይበየናል፥[ ሌሎች የሚለዉ ግራጫ ቃጭሎች፣ የስንብት ቀለማት፣ እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ እና መዳረሻዬ አፍን ይተካል]። በአዳም ስነጽሑፍ ስራዎች ላይ ርዕሰ ጉዳይ በስፋት በመተንተን አንባቢን ሊያሰለች ይችላል እንጂ ቃላትን የሚራቀቅበት ሐይል ከፈጣሪ የተሰጠዉ ይመስለኛል፤ እንደዉም በቃለመጠይቁ ላይ እምብዛም የማይስተዋለዉ እጁን ከወረቀት ስለሚያናጥቡት ነዉ።

በአዳም የስነፅሁፍ ስራዎች ላይ መቼቱ "ያ ትዉልድ" ሲሆን የአዳም ስራዎችን ተደራሲያኑ ለመረዳት ስለ ያ ትዉልድ ትንሽ ግንዛቤ ሊያደረጅ ይሻል፤ ይህም ተደራሲያኑን የዘመኑን መንፈስ እና መልክ ለመረዳት ያግዛል። በአዳም ስራዎች በስፋት በArchetypal Elements የበለጸገ ነዉ።

"An archetype (ARK-uh-type) is an idea, symbol, pattern, or character-type, in a story. It's any story element that appears again and again in stories from cultures around the world and symbolizes something universal in the human experience. Archetypes are always somewhat in question. After all, no one has studied every culture in the world – that would be impossible – so we never know for sure whether something is truly universal."

ይመስለኛል አዳም ከመባቻዉ ጀምሮ Archetypal Elements ላይ በአንክሮ ስለሚያስብበት ሐሳቡን እንዳሻዉ እያሽሞነሞነ ይገልፃል፤ መፈከር ይችልበታል። አዳም ጥቃቅን ነገሮችን በቸልታ የሚያልፍ አይደለም። ለአብነት ብናይ
ምሳሌ አንድ:- #ግራጫ_ቃጭሎች" ላይ ለመዝገቡ ግድ የሚሰጡት "ስለ ናና ከረሜላ፣ ስለጉብታ፣ ስለአበበ ቢቂላ ፎቶ እና አዲስ አበባን ከንፋስ መዉጫ ያስበለጠበት ተረኮች ነገሮች ያለዉን አስተዉሎት ላቅ ያለ ነዉ።

ምሳሌ ሁለት:- #ይወስዳል_መንገድ_ያመጣል_መንገድ" ላይ የአንድ ሰፈር ልጆች ህይወት እና ዕጣ ፈንታ 7 መንገዶች አድርጐ ይተርካል።በትረካዉ ዉስጥ የልጆቹን ዕድገት፣ ጉርምስና እና የፓለቲካ ተሳትፎአቸው ብሎም አሳዛኝ ፍፃሜን በጥንቃቄ ለሁሉም ሁነት ትኩረት ሰጥቶ ይተርካል።

"ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል፣ ከላይ ወደታች ተዟዙሬ አጥንቼአለሁ። ነገሮችን በዐይን፣ በዳሰሳ በጣዕማቸው መድቤአለሁ።

ይሄ ጎዳናዬ ነበር።
ይሄ አገሬም ነበር"

ደሃ እናቱ እንዝርቷን እያሾረች "እግሮችህ የቡሄ ጥቢኛ ይመስላሉ" ትለዋለች። ድህነት ይዟት ለእግሩ ጫማ መግዛት ስለማትችል፣ አድጎ በእግሩ መሄድ ሲጀምር ለእግሮቹ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጀምራል። የጣቶቹ ቁጥር ጎድሎ እንደሆነ ይቆጥራል፣ ጣቶቹ መሃል ያለውን አቧራ እየፈተለ ይጠርጋል። "በእናቴ የእግሮቼ ጥቢኛ ተብሎ መሰየም መንገዶችን አተኩሬ እንዳይ አደረገኝ" እያለ መንገዶቹን በልዩ አትኩሮት ይመዘግባል።

አዳም በሌላ መልኩ "ያ ዘመን" ላይ ሙጥኝ ያለ ይሆንብኛል።በበርካታ ስራዎቹ በያ ዘመን መንፈስ ጥላ ያጠላባቸዋል፤ ያ ዘመን እንዲረሳ ያልፈለገዉ አንዳች ነገር ይኖራል።[በእርግጥ ይሄን ለማለት psychoanalysis ቢያስፈልገዉም የግል ድምዳሜዬ ነዉ።]

## ሥግር ልብወለዱ- አፍ

የደራሲ አዳም ረታ የመጨረሻው ስራ አፍ ሲሆን በ2010 ዓ.ም ለንባብ በቅቷል። "አፍ" ከሌሎች የአዳም ስራዎች ለየት የሚያደርገዉ በድህረዘመናዊ ስነፅሁፍ ቅንብብ ኾኖ በቅርፅ ሐገርኛ ቀመስ የሆነ ሲሆን ይህ በራሱ ለስነጽሁፋችን አዲስ ቅርፅ በማስተዋወቅ ረገድ ወደር የለዉም፤ ይህ ምናልባት ለጀማሪ ከያኒያን ከባህርማዶ ቀድቶ ከማምጣት እንዲታቀቡ ማሳያ ነዉ።

በድህረዘመናዊ ስነጽሑፍ ዉስጥ የተለመደዉን የአፃፃፍ ስልት Deconstructed ማድረግ የተለመደ ነዉ።

"postmodern fiction has obviously changed linearity,linear causality and qualitative difference lose much of thier impact."
አዳም ረታ በ"አፍ ዉስጥ የተጠቀመባቸውን ስነፅሁፍ ዘዴዎችን ለመዳሰስ እንሞክር

### 1.ቅርጽ

የድርሰቱ ቅርፅ የተቀዳዉ ከባለ አምስት ጠጠር ቅልልቦሽ ጨዋታ ሲሆን እንደጨዋታዉ ድርሰቱም አንዱን[ጌርሳሞት] እንደመቅለቢያ ወደ ላይ አጉኖ ሌሎች አራቶች ጠጠርን[ ገለታ፣ ዘሪሁን፣ባካፋ፣ አቡ] አንድ በአንድ ይሰበስባል።መፅሐፉን ስናነብ ባለአዲስ ቅርጽ መሆኑ ባያጠያይቅም አስቀድመን ቅልልቦሽ ጨዋታ ሕግ ጋር እያስተያየን ማቅረባችን አይቀርም።አዳም ድህረዘመናዊ ስነጽሑፍ የተረዳበት እና ሐገርኛ ጣዕም ለመስጠት የሄደበት ርቀት ይብል ያሰኛል። ከባህላዊ ጨዋታ አንዱ የሆነዉ ቅልልቦሽ በዚህ ልክ አስተዉሎ እንደ አንድ ቅርፅ መጠቀም አስተዉሎት ይጠይቃል።የቅርጹ መልክ ብቻ ሳይሆን አተራረኩ Deduction method መጠቀሙ የቅርጹን ዉበት ጎልቶ አሳይቷል።

**2.የቋንቋ እንግዳነት**

በድህረዘመናዊ ስነፅሁፍ ላይ ቃላት "the bridge of realm of language and real world" በመሆኑ አዳም ረታ በዚህ ድረሰት ላይ በሰፊዉ አዲስ ቃላትን የተጠቀመ ነዉ። ይህ ምናልባትም አንባቢያን ሊያደናግር ቢችልም ነገር ግን አንባቢያን አገባባዊ ፍቺ (contextual meaning) በመስጠት ዋና መልዕክቱን ማግኘት ይቻላል።

**3. ተፋልሶ**

በአዳም ረታ በዘመን ዉስጥ ያለዉን የዘመን መልከሸ፣ የዘመን ተጋሪዎች ጋር ተቃርኖ በራስ አዉደምህረት ይብከነከናል። በገጽ (66) "መጠራጠርና መናናቅ ባለበት ቦታ መኖር አይመችም፡ ፡›› ብሎን ማህበረሰብ አወቃቀራችን እና እንደማህበረሰብ ያለንን settlement ይተቻል፤" ታከተኝ ይለናል። በቀጥሎም በገጽ (36) ላይ "
‹‹በአሉባልታ አገር ላይ ምርምር ምን ይጠቅማል?›› ይለናል።

**4.ትረካ ድባብ እና አገባብን(context based)መሰረት ያደረገ መገንዘብ**

አዳም በዚህ ድርሰት ዉስጥ ልክ እንደ ቅርጹ በአተራረከሸ ስልቱ ዉስጥ አንዱ የቅልልቦሽ ተጫዋቾች የሚኖረዉ ሚና እና ለሚቀጥለዉ ለሌላኛዉ እንደሚሰጠዉ ትረካዉንም በሁለት ከፍሎ ይተርካል። የተከፈሉትን ተረኮች ለማየት እንሞክር

**መልካ መልክ አንድ(1)**

እንደ ጨዋታዉ በመቃለቢያ ጠጠሯ( ጌርሳሞት) የታቦት ማደሪያ ሰፈር ወጣቶችን አንድን ከአንዱ እያቀላለበ በጠጠሮቹ መካከል ግን ያለመያያዝን ይተርካል።ተጫዋቹ መቃለቢያዋን ጌርሳሞት ከፍ አድርጎ በማጎኑ መሬት ያሉትን ጠጠሮች ሳይቀል እንዳንዱ ማለት ከገለታ ጀምሮ ከእጁ እንደወጡ ይተርካል።በዚህ ትረካ ዉስጥም አዳም እያንዳንዱን ሁነቶች በአንክሮ ይተርካል።

**መልካ መልክ ሁለት(2)**

በዚህ የትረካ ምዕራፍ ዉስጥ ተቀላቢዉ ጠጠር ወደ ላይ ሲያጉት space and time Continue መሰረት አድርጎ የሚኖሩትን ክዋኔዎች ይተርክልናል።

በአጠቃላይ አዳም ረታ በ"አፍ ዉስጥ metafiction፣ በይነ ዲሲፕሊናዊ ጠባይ ያላቸዉ ተረኮች(intertextuality) እና የአዳም የስነጽሑፍ ፍልስፍና የሆነዉን ህፅናዊነት የሆነ stylistic በመጠቀም ዋና ጭብጡ ግላዊ እይታ፣ አንፃራዊ አመለካከት፣ ጥበባዊ ሐሳብ፣ ዉስጣዊ ዉበት ፣ባዶ እዉነት እና ስሜታዊ ዉሸትን ልያሳየን ሞክሯል።

********

📖 አፍ (2010 ዓ.ም)
📖 ግራጫ ቃጭሎች (1997 ዓ.ም)
📖 ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ, አዳም ረታ(2003 ዓ.ም)
📖 The Cambridge Introduction to Postmodernism Fiction, Bran Nicol